ለተሳነው የትላንት፣ የዛሬውና የነገው ከጳሁ ባይ ሁሉ የሥልጣን ሽኩቻው ተሸናፊ መሆን እንድ ነገር ወደሕዝብ ጐራ በውል መመለስ ሌላ ነገር ነው የምንለው::

ለዚህ ነው በአጼው ቢተመንግሥት በሚካሄዱ የጉልቻ ለውጥ እርካታ ይመጣል ብለው የማይጠብቁ ክፍሎች፣ ለዴሞክራሲና ለነፃነት ከሕዝባዊ ትግል ሌላ መፍትሔ የለም የሚሉ ክፍሎች፣ ገና ከጠዋቱ እምነታቸውን በትግላቸው ላይ በማድረግ ከዝንጀሮ ቆንጆ ማመራረጡን ትተው ተጋድሏቸውን ከግብ ለማድረስ ሕዝቡን መሠረት ባደረገ ትግላቸው የቀጠሉት የሚቀጥሉትም:: ሕዝባዊ ትግሉ እየተፋፋመ ሲሄድ የፋሽስቶቹ ጎራ በውስጣዊ ቅራኔ ይበልጥ እየተደቆሰ እንደሚዳከምም ጥርጥር የለውም:: ትግላችን "አክራሪውን" ፋሽስት፣ በ"ለዘብተኛው" ፋሽስት፣ "አክራሪውን" ነፍሰ-ገዳይ በ"ለዘብተኛው" ነፍሰ-ጋዳይ፣ "ጭፍኑን" አምባገነን በ"ለዘብተኛ" ፈላጭ ቆራጭ ለመተካት ሳይሆን በአጠቃላይ የፋሽስቶችን ሥልጣን ለመገርሰስ፣ አምባገነናዊነትን ለማጥፋትና ሃቀኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሁም ነፃ ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ በመሆኑ ይህ ታሪካዊ ትግላችን ከግብ ሳይደርስ ከቶም የሚቋረጥ አይሆንም:: የየካቲት አብዮት በመሐል ተጨናግፎ የተከተለውን መከራ የምናውቅ በመሆናችን ከተመክሮአችን ተምረን የተያያዝነውን ትግል ኢትዮጵያን ነፃና ዴሞክራሲያዊት ሀገር እስከሚያደርግ ድረስ መግፋቱ ታሪካዊ ኃላፊነታችን ነው::

– እውነተኛውን ድል፣ ዴሞክራሲ

በሕዝቡ ትግል ብቻ ይቀዳጇል!

– ድሉም የሕዝብ ነው!!

የ ጎውፊዩ